# በማስተላለፊያ ዋጋ የሚደረግ ግብይትን ለመከላከል የወጣውን መመሪያ ለማሻሻል ስለተዘጋጀው መመሪያ የቀረበ አጭር መግለጫ

## 1. መግቢያ

በመልማት ላይ የሚገኙ አገሮች ኢኮኖሚያቸው ከሚያመነጨው ሃብት ተገቢውን ግብር እንዳይሰበስቡ እንቅፋት ከሚሆንባቸው አሰራሮች አንዱ በተለያዩ አገሮች የንግድ ስራ እንቅስቃሴ የሚያከናውኑ ኩባንያዎች (multinational companies) አንዱ ከሌላው ጋር የሚፈጽሙትን ግብይት ዋጋ በማሳነስ ወይም በማስበለጥ የንግድ ስራቸው ትክክለኛ ትርፍ ወይም ኪሳራ እንዳይታወቅ በማድረግ ግብር ላለመክፈል የሚያደርጉት ጥረት ነው።

በተመሳሳይ በአገር ውስጥ ከሚገኙ ግንኙነት ባላቸው ሰዎች ባለቤትነት ስር ካሉ ድርጅቶች አንዱ የግብር እፎይታ ያለው በሚሆንበት ጊዜ በእነዚህ ድርጅቶች መካከል የሚከናወነውን ግብይት ዋጋ በማሳነስ ወይም በማሳደግ ግብር የመክፈል ግዴታ የሌለበት ድርጅት ከፍተኛውን ትርፍ ያስመዘገበ በሚያስመስል አኳኋን ታክስ ላለመክፈል የሚደረገው ጥረት የመንግስትን ገቢ በመሸርሸር ላይ ይገኛል።

በመሆኑም በማስተላለፊያ ዋጋ (Transfer Pricing) የሚደረገውን ግብይት በመከላከል ማናቸውም ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የሚደረግ ግብይት የገበያ ዋጋን የተከተለ (Arm's Length Transaction) መሆኑን ማረጋገጥ የሚያስችል መመሪያ ቁጥር 43/2007 ወጥቶ ከ2007 ዓ.ም. ጀምሮ በስራ ላይ ቆይቷል። (231/2013 በሚል በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ ይገኛል)።

ይሁን እንጂ ይህ መመሪያ ከወጣ በኋላ ለመመሪያው መሰረት የነበረው የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 ተሽሮ ስራ ላይ ባለው የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 የተተካ በመሆኑ መመሪያው ከአዲሱ የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 79 ድንጋጌ ጋር በሚጣጣም መልኩ እንዲሻሻል ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

## 2. የማሻሻያው ዋና ዋና ገጽታዎች

### 2.1 ለመመሪያው መሰረት የሆነውን አዋጅ ቁጥር ማስተካከል

በመግቢያው እንደተገለጸው በስራ ላይ ያለው መመሪያ የወጣው የገንዘብ ሚኒስቴር በማስተላለፊያ ዋጋ የሚደረግ ግብይትን ለመከላከል የሚያስችል መመሪያ እንዲያወጣ ስልጣን በሚሰጠው የተሻረው የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 29 መሰረት ነው።

ይህ አዋጅ ተሽሮ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 የተተካ ሲሆን፤ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 79 በተመሳሳይ በገበያ ዋጋ የሚደረግ ግብይትን ለመከላከል እንዲቻል የገቢ ወይም የወጪ ድልድል የሚደረግበት ሁኔታ የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን መሆኑን ይደነግጋል።

በስራ ላይ ያለው መመሪያ ፍተሻ ከተደረገበት በኋላ ከአዲሱ የገቢ ግብር አዋጅ ጋር የሚጣጣም ሆኖ በመገኘቱ መጠነኛ ማስተካከያዎችን እንዲሁም የመመሪያው የስልጣን መሰረት አዲሱ የገቢ ግብር አዋጅ እንዲሆን በማድረግ የመመሪያው ተፈጻሚነት እንዲቀጥል ተደርጓል።

### 2.2 የመመሪያው አንቀጽ 2 (5) (ረ)

በማስተላለፊያ ዋጋ ግብይትን በመፈጸም ሊከፈል የሚገባውን ግብር የማሳነስ ወይም ጨርሶ ግብር እንዳይከፈል ለማድረግ ጥረት የሚደረገው ግብይቱ ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የተፈጸመ በሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡

ይህም በመሆኑ ግብይትን የሚተረጉመው የመመሪያው አንቀጽ 2(5) (ረ) ይህንን በትክክል በሚያንጸባርቅ መልክ እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡

### 2.3 የመመሪያው አንቀጽ 16

በማስተላለፊያ ዋጋ ግብይት የሚፈጸመው በተለያዩ አገሮች ያለው የግብር ማስከፈያ መጣኔ የተለያየ ሲሆን ወይም አንደኛው አገር ጭራሹንም ታክስ የማያስከፍል በሚሆንበት ጊዜ ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ግብር ከፍዩ ባገኘው ትርፍ ላይ ሊከፍል የሚገባውን ትክክለኛውን ግብር እንዳይከፍል ለማድረግ ነው፡፡

በመሆኑም ገቢው በተገኘበት አገር ትክክለኛው ግብር እንዲከፈል ለማድረግ የሁለቱንም ተገበያዮች ወጪ ወይም ገቢ ማስተካከል ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም የመመሪያው አንቀጽ 16 ግብይቱ የአገር ውስጥ በሚሆንበት ጊዜ ማስተካከያው የሚደረገው በሁለቱም ታክስ ከፋዮች ሂሳብ ላይ መሆኑን ግልጽ እንዲሆን እና ትክክለኛው የአዋጁ አንቀጽ እንዲጠቀስ ተደርጓል፡፡

### 2.4 የመመሪያው አንቀጽ 19

ግብር ከፋዮች ግብይቱ በገበያ ዋጋ የተፈጸመ መሆኑን የሚያስረዱ ማስረጃዎችን እንዲይዙ የሚጠበቅባቸው ቢሆንም ይህንን በመፈጸም ረገድ ከፍተኛ ቸልተኝነት ይታያል፡፡

በመሆኑም በአዋጁ እና በመመሪያው የተዘረዘሩ መዛግብትን ያልያዙ ግብር ከፋዮች በታክስ አስተዳደር አዋጁ መዝገብ ስላለመያዝ የተደነገገውን ቅጣት የሚቀጡ መሆኑን የሚገልጽ አንቀጽ ታክሏል፡፡